# ዝምታህ ጨኸብኝ !






አንተ ፀጥ ያልከው ሰው - አንት የተሎጎምከው
አጥርህ ዙሪያ ታጥሮ - በርክን የዘጋኸው
ከሰው መሃል ሆነህ - ከሰው ልጅ የራቅከው
ለምስጋናም አሜን
ለእርግማንም አሜን
አሜን በፀጥታህ - አሜን አሜን ያልከው
ዝምታህ ጨኸብኝ - ጆሮዬን በጠሰው
እባክህ ተናገር - ዝምታህም ያብቃ
ዝምታ ትብብር - ከበዳይ አለቃ
መሆኑን እወቀው - የዝምታ ደሞዝ
ዝምታ ጠላት ነው - ይኸን እወቅ ጎበዝ።



ነጎድጓድ ባልሰማም - የመብረቅ ብልጭታ
የአውሎ ነፋስ ጩኸት - የዝናብ እሩምታ
መርዶን - ተከትሎ - ደረት ባይመታ
“ወየው ወይኔ!” ባይኖር እንባም መንታ መንታ
ዝምታ ረብሻ ነው - ከጩኸት የበዛ
ህሊናን በጭንቀት - ሰው በአሳር የገዛ።



አወይ ገለልተኛ - አወይ ትርምሱ - አወይ ግሳንግሱ
የዝምታ ጓዙ - በየትኛው ድልድይ - ይሻገራል እሱ
ከእኛ አሚባል እኛ - አሻግሮ የሚያይ ጠፍቶ
ልዩነት ይታያል - ከአንድነቱ ጎልቶ
አወይ ገለልተኛ - ምነዋ አንናገር - አንደበት ተዘጋ
ለአገራችን ጉዳይ - ማንስ ለእኛ ያውጋ
ምነው ዝም የምንል - ህዝብ እየተወጋ?





አሜን በፀጥታህ - አሜን አሜን ያልከው
ዝምታህ ጨኸብኝ - ጆሮዬን በጠሰው
እባክህ ተናገር - ዝምታህም ያብቃ
ዝምታ ትብብር - ከበዳይ አለቃ
መሆኑን እወቀው - የዝምታ ደሞዝ
ዝምታ ጠላት ነው - ይኸን እወቅ ጎበዝ።

ዳግማዊ ዳዊት
ግንቦት 2002 ዓ.ም.
Ethio_dagmawi@yahoo.com